# ኢንፍሎዌንዛ(ወረርሽኝ) ልጅህ በበሽታው በሚጠቃበት ወቅት

## ልጅህበወረርሽኙተጠቅቶበሚታመምበት ወቅት



እድሜያቸው ከአምስት ዓመት (5) በታች የሆኑ ህፃናት በበሽታው በይበልጥ የመጠቃት እድል አላቸው። በአስምና በስኳር በሽታ ለረጅም ጊዜ የተጠቁ ህፃናትም በወረርሽኙ ሲያዙ ችግራቸው የበረታ ይሆናል።

ልጅህ ከአምስ ዓመት(5) እድሜ በታች ከሆነና ለረጅም ጊዜ በሚቆይ (እንደ አስምና ስኳር በሽታ) ተጠቂ ከሆነና የወረርሽኙ ምልክቶች ከታዩበት ስቃዩ እንደሚበረታበት ይታወቃል።

ልጅህ ምርመራ ሊደረግለት ያስፈልግ  እንደሆን ለማወቅ ሐኪምህን አማክረው።



ብዙዎቹ ህፃናት ወደ ሐኪሙ ከመሄዳቸው በፊት ህመሙ ይለቃቸዋል።ሌሎች ደግሞ የወረርሽኙ ስቃይ ሊበረታባቸው ይችላል። በማንኛውም የእድሜ እርከን የሚገኝ ህፃን የወረርሽኙ ምልክቶች ከታዩበት ወደ ሐኪም መሄድ አለበት።



የፀረ-ቫይረስ መድሃኒቶች ህመሙ በተከሰተ በሁለት ቀናት (48 ሰዓታት) ቢወሰዱ ውጤታማ ይሆናሉ።

ልጅህ ወደ ሆስፒታል ከተወሰደ ወይም በወረርሽኙ በመጠቃቱ ለበለጠ ህመም የሚዳረግ ከሆነ ሐኪሙ ከ48 ሰዓታት በኋላም ቢሆን የፀረ- ቫይረስ መድሂኒቱን ሊሰጠው ይችላል።

# ኢንፍሎዌንዛ(ወረርሽኝ) ልጅህ በበሽታው በሚጠቃበት ወቅት

ትኩሳት የሚከሰተው የሰውነት ሙቀት ከ100 ዲግሪ ፋራናይት (37 ዲግሪ ሴንቲግሬድ) በላይ ወይም (እኩልሲሆንነው።የቴርሞሜትር መሣሪያከሌለህ የልጅህን ፊት ዳብሰው። ልጅህ ከመካከኛው መጠን ያለፈ ትኩሳት ከታየበት፣ ፊቱ ከቀላ፣ የማላብና የመንዘፍዘፍ ወይም የማንቀጥቀጥ ስሜት ከታየበት ትኩሳት ሊኖርበት ይችላል ማለት ነው።



ልጅህ ትኩሳት ከታየበት ትኩሳቱን ለመቀነስ የምንጠቀምባቸው መድሃኒቶች አሉ። አንዳንዶቹ በመድሃኒት መሸጫ ቤቶች ይገዛሉ። ያለአንዳች ጥያቄ መግዛት ትችላለህ። አንዳንዶቹ የሐኪም ትእዛዝ ይፈልጋሉ። ከሐኪሙ ጋር መነጋገር አለብህ የልጅህን እድሜ በመገንዘብ ሐኪሙ የሚያዘውን መድሃኒት ለመግዛት ሞክር፣



በመድሃኒት ቤቶች የሚሸጡት መድሃኒቶች ህፃናትን እንደሚያሽሏቸው የሚገመቱ ናቸው። ሐኪምን በማማከር መድሃኒቶቹ ለልጅህ ተገቢ መሆናቸውን አረጋግጥ፣ ፣ ወረርሽኙ ለተጠቃው ልጅህ በምንም ዓይነት መንገድ እስኘሪን የተባለው መድሃኒት እንዳይሰጠው ተጠንቀቅ።



የዩናይትድእስቴትስየጤናጥበቃና ሰብአዊ እርዳታአገልግሎቶች መምሪያ።
የበሽታመከላከያናመቆጣጠሪያ ማእከል።

# ኢንፍሎዌንዛ(ወረርሽኝ) ልጅህ በበሽታው በሚጠቃበት ወቅት

የእክምና እርዳታ እንዲያገኝ ካልሆነ በስተቀር ትኩሳቱ እስኪለቀው ድረስ ልጅህን በቤት እንዲቆይ አድርግ።ይህንንም በማድረግህ በሽታው እንዳይስፋፋ ያረዳል።



ትካስቱ ከለቀቃቸው ከ24 ሰዓት በኋላ ህፃናቱ ወደ ትምህርት ቤት ሊሄዱ ይችላሉ። ትኩሳቱን ዝቅ የሚያደርግ መድሃኒት ሳይሰጣቸውም ቢሆን።



ልጅህ በሚታመምበት ጊዜ በቂ እረፍትና ሰውነቱ የሚያስፈልገውን ፈሳሽ እንያገኝ ውሃና የተለያዩ ፈሳሽ (እንደ ውሃ፣ መረቅ፣ ፈሳሽ ተኪው ስፖርትስ የሚባለው መጠጥ፣ የልጆች ኤሌክተሮላይት መጠጦች፣ Pedialyte® የመሳሰሉ) መጠጦችን አቅርብለት።



# ኢንፍሎዌንዛ(ወረርሽኝ) ልጅህ በበሽታው በሚጠቃበት ወቅት

## ወረርሽኙ በቤትህ ለሚገኙ ሌሎች ሰዎችከመሰራጨት የምትከላከልበት መንገድ አለ። ይኸውም



ልጅህ በተለየ ክፍል እንዲተኛ በማድረግ ከሌሎች ጤናማ የቤተሰቡ አባላት ግንኙነቱ የተገደበ እንዲሆን ማድረግ።



ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዳይመገብና እንዳይጠጣ ማድረግ። አንድ ሰው ብቻ እንዲንከባከበው መመደብ።



ቢቻል የሚንከባከበው ሰው ለወረርሽኙ የተጋለጠ እንዳይሆን ማድረግ።በወረርሽኙ ከተጠቃ ከባድ ችግር ውስጥ ሊገባ የሚችል እንደ አስም ያለበት ሰው ወይም እርጉዝ ሴት ለዚህ የእንክብካቤ ስራ አይፈለጉም።

ለበለጠ መረጃ የበሽታ መከላከያ ማእከልን በ800-ሲ.ዲ.ስ-ኢንፎ (232-4636) ቴሌፎን ወይም www.cdc.gov/flu. ድረ-ገጽ ተጠቀም።

የዩናይትድእስቴትስየጤናጥበቃና ሰብአዊ እርዳታአገልግሎቶች መምሪያ።
የበሽታመከላከያናመቆጣጠሪያ ማእከል።